**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ**

**የማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀት የአሠራር መመሪያ**

**ቁጥር 137/2015**

የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ የሚገባ በመሆኑ፤

የከተማውን ነዋሪዎች ደህንነትና ምቾት የተጠበቀበት በተለይም የህፃናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና ሌሎች ተጎጂ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የተለየ ድጋፍ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭና ተጎጂዎች ከሚያደርገው ጥበቃ፣ ድጋፍና ክብካቤ ባሻገር የማህበረሰብ ድጋፍ እና ክብካቤን ለማጠናከር መንግስት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት፣ የንግዱ እና መላው የህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሲኖራቸው ስለሚገባው ሚና እና እነዚህ አካላት የሚያደርጉትን ሀብት የማሰባሰብ አስተዋፅኦ በተቀናጀ መንገድ መምራት በማስፈለጉ፤
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ የአስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማቋቋምና ሥልጣና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ጉዳዮች

1. **አጭር አርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀት የአሠራር መመሪያ ቁጥር 137/2015“ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤
   2. **"አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
   3. **"ክንቲባ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክንቲባ ነው፤
   4. **"ምክር ቤት"** ማለት በከተማ፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳ እና በብሎክ ደረጃ የተቋቋመ ማህበረሰብ አቀፍ አደረጃጀት ነው፤
   5. **"ብሎክ"** ማለት ከወረዳ ቀጥሎ ከ50-150 አባወራዎች ወይም እማውራዎች የያዘ አነስተኛ የመኖሪያ አካባቢ ነው፤
   6. **"ጥምረት"** ማለት በከተማ፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በብሎክ ደረጃ በዚህ መመሪያ መሰረት ከተለያዩ አደረጃጀቶችና ከማህበረሰቡ የተውጣጣ የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤን የሚያከናውን አካል ነው፤

7. **"በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች"** ማለት ለችግር ተጋላጭ የሆኑ አረጋውያን፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሴቶች፣ ህፃናት፣ ወጣቶች፣ በልመና ላይ የተሠማሩ ሰዎች፣ ጎዳና ተዳዳሪዎች፣ የአዕምሮ ህሙማን፣ የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚዎች እንዲሁም በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ያሉ ሰዎች ማለት ነው፤

8. **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ በየደረጃው የተቋቋሙ ምክር ቤቶችን በአሰተባባሪነት የሚመራ አካል ነው፤

9. **"ጠቅላላ ጉባኤ"** ማለት ምክር ቤቱን የመሰረቱት የሁሉም አባላት የጋራ ስብሰባ ወይም ጉባኤ ነው፤

10. **"ድጋፍ"** ማለት ለማህበራዊ ችግር ተጋላጭ የሆኑ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍና ለማቋቋም የሚደረግ ተግባር ነው፤

11. **"መዋጮ"** ማለት ከማህበሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት አባላትና ከተለያዩ በጎ ፍቃደኞች የሚሰበሰብ ገንዘብ፤ ቁሳቁስ እና ሙያዊ ድጋፍ ነው፤

12. **"ሰው"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **<u>የጾታ አገላለጽ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በማህበረሰበ አቀፍ ጥምረት እንክብካቤ አደረጃጀት በሁሉም መዋቅር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5. **<u>መርሆዎች</u>**

- በጎ-ፈቃደኝነት
- ሰብዓዊነት
- ሚስጢራዊነት
- ግልጽነት
- ፍትሃዊነት
- አሳታፊነት
- ተጠያቂነት
- የህዝብን አቅምና ሀብት መሰረት ማድረግ
- የጠባቂትን ስሜት ማስወገድ
- ቅንጅታዊ አሠራርን መከተል

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት

6. **መቋቋም**

የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ምክር ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ በክፍለ ከተማ፣ በወረዳና በብሎክ ደረጃ ሕጋዊ ሰውነት አግኝቶ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

7. **አደረጃጀት**

1. በየደረጃው የተቋቋመው የጥምረቱ ምክር ቤት የሚከተለው አደረጃጀት ይኖረዋል፡-
   - ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ
   - ለ. አስተባባሪ ኮሚቴ
   - ሐ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
   - መ. የቴክኒክ ንዑሳን ኮሚቴዎች
   - ሠ. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ
2. የጥምረቱ ምክር ቤት ጠቅላላ ጉባዔ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ የወረዳና የብሎክ የማህበረሰብ-አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ቋሚ አባላት ያካተተ ይሆናል፤
3. ከብሎክ አደረጃጀት በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ "2" የተደራጀው ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥራ አመራሮች /አስተባባሪዎች/ በየደረጃው በሚገኙ አስተዳደር እርከኖች ይኖሩታል፡-
   1. የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ................................ ሰብሳቢ
   2. የሕብረተብ ተሳትፎ አደረጃትና የስራ እድል ፈጠራ አስተባባሪ ኤጀንሲ.......................................................................ም/ሰብሳቢ
   3. የጤና ቢሮ ኃላፊ ................................................................. አባል
   4. የፍትህ ቢሮ ኃላፊ ................................................................. አባል
   5. ፋይናንስ ቢሮ ........................................................................ አባል
   6. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትረስት ፈንድ .............................. አባል

8. **የከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ አመሰረራረት**

1. ጥምረቱ ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ሴቶችና ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ይሆናል፡፡
2. ጥምረቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች

   i. የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ..................... ሰብሳቢ
   ii. የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ አጄንሲ ..........................ም/ሰብሰቢ
   iii. ጤና ቢሮ ኃላፊ ...... ...................................... አባል

iv. የትምህርት ቢሮ ተወካይ ........................................ አባል

v. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማህበራዊ ትረስት ፈንድ.................................................................. አባል

vi. የፋይናንስ ቢሮ ...................................................... አባል

vii. ፍትህ ቢሮ ........................................................... አባል

ሰ. የአስራ አንዱም ክፍለ ከተማ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎች ፀሃፊዎች..... ....................አባል

ሐ. የከተማው ሲቪክ ማህበራት ....................................... አባላት፡-

i. የእድር ምክር ቤት ሰብሳቢ

ii. የአረጋውያን ማህበራት ሰብሳቢ

iii. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ሰብሳቢ

iv. የሴቶች ማህባር ሰብሳቢ

v. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ

vi. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ..................... አባል

9. <u>**የጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት**</u>

የአዲስ አበባ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. በአመት ሁለት ጊዜ ስብሰባውን ያደርጋል፤
2. የከተማውን ጥምረት ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቀል ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የግማሽ አመት እና አመታዊ የኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል ያፀድቃል፤ የማስተካከያ እርምጃዎች ይወስዳል፤
4. በኦዲት ሪፖርት መሠረት ጉድለት የታየባቸውን በየደረጃው የሚገኙ ጥምረት ኮሚቴዎችና አባላት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤ በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
5. አዳዲስ የገቢ ምንጮች ሀሰቦች ሲቀርቡ ተወያይቶ በማጽደቅ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
6. የክፍለ ከተማ፣ ወረዳና ብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረትን ሲያሻሽሉ ሲያሳድጉ የሚችሉ አዳዲስ አሰራሮች ላይ በመወያየት ማጽደቅ፤
7. የስራ አመራርና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ይሰይማል ይሽራል፤
8. የጥምረቱን አሰራር መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፤ ደንቡን መሠረት በማድረግ ውሳኔዎች ያስተላልፋል፤
9. ለማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሃሳቦች ያመነጫል ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

10. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የጥምረቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ያደርጋል፤

11. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የሃብት ምንጮችናንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሳል፤ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤

12. በከተማ ሐብት ለማሰባሰብ የሚያስችሉ ዘዴዎች እንዲቀየሱ ያደርጋል፣ ስለመሰባሰቡና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን ይከታተላል፤

10. <u>**የከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ስራ አስፈፃሚ አመሰራረት**</u>

1. ተጠሪነቱ ለአዲስ አበባ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡
2. የከተማ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. የሴቶች ህፃናት ማህበራዊ ጉዳይ ም/ቢሮ ኃላፊ .......................... ሰብሳቢ

ለ. የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ አጄንሲ ም/ዳይሬክተር ...................... ም/ሰብሰቢ

ሐ. በከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከክፍለ ከተማ ከተወከሉት አንዱ የሚመረጥ ............................... ፀኃፊ

መ. ጤና ቢሮ ተወካይ ........................................................... አባል

ሠ. ፍትህ ቢሮ ተወካይ............................................................... አባል

ረ. የፋይናንስ ቢሮ ተወካይ ......................................................... አባል

ሰ. የኃይማኖት ተቋማት ህብረት ም/ሰብሳቢ ..................................... አባል

ሸ. የዕድሮች ምክር ቤት ም/ሰብሳቢ ...............................................አባል

ቀ. የሴቶች ማህበር ም/ሰብሳቢ .....................................................  አባል

በ. በከተማ ደረጃ የሚሠሩ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች .................   አባል

ተ. የከተማ አረጋውያን ማህበር ም/ሰብሳቢ ......................................  አባል

ቸ. የከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበረሰብ ም/ሰብሳቢ ..........................  አባል

ኀ. የከተማ ወጣቶች ማህበር የሚወከል............................................. አባል

11. <u>**የከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ስራ አስፈፃሚ ስልጣንና ተግባር፡-**</u>

1. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ያፀድቃል ይተገብራል የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤
2. ዓመታዊ ኦዲት ያስደርጋል፤ ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት በማቅረብ ያፀድቃል፤
3. በየክፍለ ከተማው የተለያዩ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የገጠማቸውን የህብተሰብ ክፍሎች በክፍለ ከተማ ጥምረት እንዲለዩ ያደርጋል፤
4. ከክፍለ ከተማ የተሰበሰበውን መረጃ በማጠናከር እንደችግሩ ስፋት ለከተማው ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ እንዲፈቱ ያደርጋል፤ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
5. ከተለያዩ አካላት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የሚውሉ የፋይናንስ፣ የዓይነት፣ የእውቀትና የጉልበት ሃብቶች ያሰባስባል፤

6. በክፍለ ከተማው የደረሰውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግርን መሠረት በማድረግ ከሠበሰበው ሀብት ክፍፍል ያደርጋል፤
7. ለክፍለ ከተሞች በተደረገው ድጋፍና በክፍለ ከተማው የተሰበሰበው ሃብት በተገቢው ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ ሪፖርት እንዲደረግለት ያደርጋል፤
8. በከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ይከፍታል፤
9. የተሰበሰበ ሐብት በገቢና ወጪ አርዕስት መሠረት መረጃ እንዲደራጅ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
10. የክፍለ ከተማና ወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈፃሚዎችና አመራሮች የተለያዩ አቅም ግንባታ ስልጠናዎች የልምድ ልውውጥ እንዲያገኙ ያድርጋል፤
11. ለክፍለ ከተማው፣ ለወረዳውና ለብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አሠራር መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሃሳቦች ያመነጫል ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
12. የአጋርነት የጥምረት ግንኙነት ሥራዎች ይፈፅማል፤
13. የየጥምረቱ የከተማው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ መተዳደሪያ ደንብ ያዘጋጃል፤በምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ እንዲሻሻል ያደርጋል፤ መተዳደሪያ ደንቡን መሠረት በማድረግ ውሳኔዎች ያስተላልፋል፤
14. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሂሳብ መዛግብትን ይይዛል፤
15. የአባላት ዝርዝር መረጃዎች ወቅታዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነት የህብረተሰብ ክፍሎችን ዝርዝር በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ይይዛል
16. በተጨማሪም በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ይከናውናል፡፡

12. <u>**የከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የስራ አስፋጻሚ ሴክተር መስሪያ ቤቶች አስተባባሪ ኮሚቴ አመሰራረት**</u> ፡-

የከተማ ሥራ አስፈፃሚ አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. ተጠሪነቱ ለከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፤
2. የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ ኃላፊ ............................ሰብሳቢ
3. የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ኤጄንሲ ዳይሬክተር ..............ም/ሰብሳቢ
4. ፍትህ ቢሮ ም/ኃላፊ ........................................................ አባል
5. ፋይናንስ ቢሮ ም/ኃላፊ ...................................................... አባል
6. በክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና አንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ አምስት አባላት አንዱ የሥራ አስፈጻሚ ፀሐፊ ................................ አባል

13. <u>**የከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሴክተር መስሪያ ቤቶች ስራ አስፋጻሚ አስተባበሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**</u>

1. የጉባኤውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤
2. የኮሚቴ አባላት የሆኑ አስፈጻሚ አካላት ተሳትፎ እንዲጠናከር ያደርጋል፤
3. ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፣
4. ድጋፍ ሲያገኙ የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀናጠፈ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲጠና በማድረግ ለጉባኤው ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤

14. <u>**የከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሴክተር መስሪያ ቤቶች ስራ አስፋጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሰብሳቢ**</u>

የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል:-

1. ተጠሪነቱ ለከተማው ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤
2. የጥምረቱን አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሥራና በጀት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤
3. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል ፣ ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፤
4. ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፣ ድጋፉም እንዲደርሳቸው ክትትል ያደርጋል፤
5. ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው የማጠናከር ፣ መከታተልና ድጋፍ እንዲያገኙ ለምክር ቤቱ ያሳውቃል፤
6. የሐብት ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ከማዕከል እስከ ብሎክ የሚካሄደውን ስርጭት የፋይናንስ ህግ ስርዓት ተከትሎ መፈፀሙንና ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል፣ ይደግፋል ያስተባብራል፤
7. የከተማው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ከባንክ አካውንት ላይ በጣምራ ይፈርማል፤
8. የከተማው የማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሃብት ማሰባሰብ ሂደቶችን በጥብቅ ዲሲፒሊን እንዲመራ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል መጠኑንና ዓይነቱን ይለያል፤
9. የአስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶችን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ስብሰባ ይጠራል ውሳኔዎችን ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፤
10. በክፍለ ከተማው ድጋፍ የሚሹ የማህበራዊ ችግር ተጎጂ የሆኑ ህፃናትን ሴቶችን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የተለዩበትን አግባብ መረጃ አያያዙን ይመረምራል፤ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፤
11. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው ያጠናክራል ፣ይከታተላል ፣ይደግፋል፣ ያስተባብራል፡፡

15. <u>**የከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ**</u>

የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል:-

1. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ለሴክተር መስሪያ ቤቶች አስተባባሪ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፤
2. የሴክተር መስሪያ ቤቶች አስተባባሪ ሥራ አስፈጻሚው ዋና ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
3. በየበጀት ዓመቱ የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን የጉልበት እና እውቀት የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት በምክር ቤት ያፀቅዳል፤
4. ለሥራ አስፈጻሚው የተሰጡ ተግባራትን በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይፈጸማል ለለክንውኑ ሪፖርት ያቀርባል፤
5. አረጋውያን ለወጣቶች ልምዳቸውን የሚያከፍሉበትንና ወጣቶቹ ደግሞ የተለያዩ የእንክብካቤና የድጋፍ ተግባራትን የሚያከናውኑበትን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የትምህርትና ሙያ ሥልጠና እድል ለማግኘት ያልቻሉ ሥራ አጥ ወጣቶችን ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ችግራቸውን ለመፍታት መረጃቸውን አደራጅቶ ለሥራ አስፈጻሚው ያቀርባል ፤ይከታተላል ፤አፈጻጸሙን ሪፖርት ያቀርባል፤
7. የከተማው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ከባንክ አካውንት ላይ በጣምራ ይፈርማል፡፡

16. <u>**የከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ፀሐፊ**</u> የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል :-

1. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሰብሳቢ ይሆናል፤
2. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት መረጃዎች ፤ቃለ-ጉባዔዎች አስፈላጊ ሰነዶችን ያደራጃል፣ በአግባቡ ይይዛል፤ ሲጠየቅም ያቀርባል፤
3. የከተማውን የብሎክ ነዋሪዎች ዝርዝር መረጃ (PROFILE) አደራጅቶ ይይዛል፤
4. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ድጋፍ ፈላጊዎች በየጊዜው መረጃዎችን ያደራጃል ለሰብሳቢው ያቀርባል፤
5. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ማህተም በጥንቃቄ ይይዛል፤
6. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ከየብሎኩ በስፋት የሚነሱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአጀንዳ መካተቱን በማረጋገጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤
7. የከተማው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ከባንክ አካውንት ላይ በጣምራ ይፈርማል፤
8. የስብሰባ ጥሪዎችንና ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል::

17. <u>የከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት</u>

1. የጤና ቢሮ

ጤና ቢሮ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፤

ለ. በበጀት ዓመቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭ የሆኑና በደማቸው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ ያለባቸውን መሰረት አድርጎ ያቅዳል፣ ያጸድቃል፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል ፣

ሐ. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፤

መ. ድጋፍ የሚሹ ኤች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን መረጃ ያደራጃል ለምክር ቤቱ ያቀርባል ያጸድቃል፣ አሰራሩን ተከትሎ ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ድጋፍ እንዲደረግላቸው ክትትል ያደርጋል፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2. የፋይናንስ ቢሮ

ፋይናንስ ቢሮ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል:

ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፤

ለ. የጥምረቱ ገቢና ወጪ የፋይናንስ አሰራር የተከተለ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ. የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፤

መ. ለከተማ፣ ክፍለ ከተማ በሥሩ ለሚገኙ ወረዳዎችና ብሉክ ጥምረቶች የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ያሰራጫል፤

ሠ. ከፍተኛ የሀብት ምንጭ ካለባቸው የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ድህነት ወደ ከፋባቸው የብሉክ ጥምረቶች ሀብት የሚዘዋወርበትን መንገድ ይቀይሳል፤

ረ. የከተማ፣ የክፍለ ከተማና ወረዳ ጥምርት ሂሳብ በራሱ ባለሙያዎች ኦዲት ያደርጋል፤ በተጨማሪም በውጪ ኦዲተርም እንዲያስደርጉ ደርጋል፡፡

3. ፍትህ ቢሮ

ፍትህ ቢሮ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል:-

ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፤

ለ. በከተማ ደረጃ የማህበራዊ ችግር ተጋላጮቾች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ይቀበላል ትክክለኛነት ይመረምራል ለቅሬታው ምላሽ ይሰጣል፤

ሐ. የማህበራዊ ችግር ተጋላጮችች ልዩታ ምልመላና መረጣ የድጋፍ አሰጣጥ ፍትሃዊነት ያረጋግጣል፤

መ. የሀብት አሰባሰቡን እና አጠቃቀሙን ፍትያዊነት ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኝ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፤

18. <u>**የክፍለ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ አመሰራረት፤**</u>

የክፍለ ከተማ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. አስተባባሪ ሴክተር ጽህፈት ቤቶች
   - ሀ. የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ኃላፊ .................. ሰብሳቢ
   - ለ. የሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት .......................... ም/ሰብሰቢ
   - ሐ. ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ ..................................................... አባል
   - መ. የፋይናንስ ጽ/ቤት ......................................................... አባል
   - ሠ. ፍትህ ጽ/ቤት................................................................ አባል
2. ከወረዳው ማህበረሰብ ዓቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጡት መሐል ........................................................ ፀሐፊ
3. በክፍለ ከተማው ማህበረሰብ ዓቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ አራት ሰዎች ....................................................... አባላት
4. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ወረዳዎች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊዎች ........ አባል
5. የክፍለ ከተማ ሲቪክ ማህበራት አባላት
   - ሀ. የኃይማኖት ተቋማት ሰብሳቢ
   - ለ. የእድር ምክር ቤት ሰብሳቢ
   - ሐ. የአረጋውያን ምክር ቤት ሰብሳቢ
   - መ. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ሰብሳቢ
   - ሠ. የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ
   - ረ. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ
   - ሰ. በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች (CSOs)
   - ሸ. የተዋቂ ግለሰቦች ተወካዮች
   - ቀ. የንግዱ ማህበራሰብ ተወካይ ናቸው::
6. እንደ አስፈላጊነቱ በየደረጃዉ ተጨማሪ የኮሚቴ አባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡

19. <u>የክፍለ ከተማ የማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ  ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>

1. በሰብሰቢው በሚደረግ ጥሪ በዓመት ሁለት ጊዜ ስብሰባውን ያደርጋል፤
2. የጥምረቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤የአፈጻፀም ሪፖርት ያዳምጣል ያፀድቃል፤
3. የግማሽ ዓመትና ዓመታዊ ኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፤ ያጸድቃል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤
4. በኦዲት ሪፖርት መሠረት ጉድለት የታየባቸውን የክፍለ ከተማውን፣ የወረዳውንና የብሎኩን ጥምረት አባላት ላይ እርምጃ ይወስዳል በህግ አግባብ እንዲጠየቁ ያደርጋል፤
5. እንደ አስፈላጊነቱ  ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ይሰይማል፤ ይሸራል፤
6. ለክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሐሳቦች ያመንጫል በከተማው ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ሲፈቀድ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
7. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የሐብት ምንጮችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሳል፤ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱም ይከታተላል፤  በከተማው ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

20. <u>የክፍለ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ስራ አስፈጻሚ አመሰራረትና ተጠሪነት፤</u>

ተጠሪነቱ ለከተማው ጥመረት እና ለክፍለ ከተማው ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፤

የክፍለ ከተማ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክፍለ ከተማው ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሚመደብ ተወካይ .................. ሰብሳቢ
2. የክፍለ ከተማው  ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተወካይ .......... ምክትል ሰብሳቢ
3. በየክፍለ ከተማው  ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጡት ውስጥ ................. ፀሐፊ
4. ከጤና ጽህፈት ቤት የሚመደብ ተወካይ  ....................................... አባል
5. ከትምህርት ጽህፈት ቤት የሚመደብ ተወካይ  .................................. አባል
6. ከፍትህ ጽህፈት ቤት የሚመደብ ተወካይ  ..................................... አባል
7. በየክፍለ ከተማው  ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የሚመረጡ አራት ሰዎች .................. አባል
8. የክፍለ ከተማው ሃይማኖት ተቋማት ህብረት ምክትል ሰብሳቢ .........  አባል
9. የክፍለ ከተማው ዕድሮች ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ ..................  አባል
10. የክፍለ ከተማው ሴቶች ማህበር ምክትል ሰብሳቢ ........................... አባል
11. በክፍለ ከተማው የሚገኙ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች..................... አባል
12. የክፍለ ከተማው አረጋውያን ማህበር ምክትል ሰብሳቢ ..................  አባል
13. የክፍለ ከተማው የአካል ጉዳተኞች ማህበር ምክትልሰብሳቢ .............. አባል

14. የክፍለ ከተማው የወጣቶች ምክትል ማህበር ................................ አባል

15. የክፍለ ከተማው የታዋቂ ግለሰቦች ተወካይ ...................................አባል

16. የንግዱ ማህበራሰብ ተወካይ ..................................................... አባል

17. እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ አባላት ሊኖሩት ይችላሉ፡፡

21. **<u>የክፍለ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈፃሚ ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>**

1. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል ያፀድቃል ይተገብራል የአፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባል፤
2. ዓመታዊ ኦዲት ያስደርጋል ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት በማቅረብ ያፀድቃል፤
3. በየክፍለ ከተማው የተለያዩ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የገጠማቸውን የህብተሰብ ክፍሎች ይለያል፤
4. ከወረዳ የተሰበሰበውን መረጃ በማጠናከር እንደችግሩ ስፋት ለከተማው ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ እንዲፈቱ ያደርጋል፤ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
5. ከተለያዩ አካላት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የሚውሉ የፋይናንስ፣ የቁሳቁስ፣ የእውቀትና የጉልበት ሃብቶች ያሰባስባል፤
6. በወረዳው የደረሰውን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግርን መሠረት በማድረግ ከሠበሰበው ሀብት ክፍፍል ያደርጋል፤
7. ለወረዳው በተደረገው ድጋፍና በወረዳው የተሰበሰበው ሃብት በተገቢው ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ ሪፖርት እንዲደረግለት ያደርጋል፤
8. የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካውንት ይከፍታል፤
9. የተሰበሰበ ሐብት በገቢና ወጪ አርዕስት መሠረት መረጃ እንዲደረጅ ያደርጋል፤ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
10. ለወረዳና ለብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈፃሚዎችና አመራሮች የተለያዩ አቅም ግንባታ ስልጠናዎች የልምድ ልውውጥ እንዲያገኙ ያድርጋል፤
11. ለወረዳውና ለብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አሠራር መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሃሳቦች ያመነጫል ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
12. የአጋርነት የጥምረት ግንኙነት ሥራዎች ይፈፅማል፤
13. የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሂሳብ መዘግብት ይይዛል፤
14. የአባላት ዝርዝር መረጃዎች ወቅታዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነት የህብረተሰብ ክፍሎችን ዝርዝር በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ይይዛል፡፡
15. በጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ስራች ያከናውናል፡፡

22. **<u>የክፍለ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ የአስተባባሪ ሴክተር መስሪያ አባላት:-</u>**

1. ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ................... ሰብሳቢ
2. ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ..................... ምክትል ሰብሳቢ

3. በየክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጡት ውስጥ ................................................................ ፀሐፊ
4. ጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ........................................................... አባል
5. ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ................................................... አባል
6. ፍትህ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ........................................................ አባል
7. ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ .......................................................አባል

23. <u>የየክፍለ ከተማ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሴክተር መስሪያ ቤቶች ስራ አስፈጻሚ አስተባበሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የጉባኤውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤
2. የኮሚቴ አባላት የሆኑ አስፈጻሚ አካላት ተሳትፎ እንዲጠናከር ያደርጋል፤
3. ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፣
4. ድጋፍ ሲያገኙ የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀላጠፈ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲጠና በማድረግ ለጉባኤው ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤

24. <u>የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ</u> የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፤
2. የጥምረቱን አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሥራና በጀት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ የሥራ አስፈፃሚውን ኮሚቴ በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፤ ስለአፈፃፀሙ ሪፖርት ያቀርባል፤
3. የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል ፤ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፣
4. በክፍለ ከተማ ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፣ ድጋፉም እንዲደርሳቸው ክትትል ያደርጋል፤
5. ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው የማጠናከር ፤መከታተልና ድጋፈ እንዲያገኙ ለከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አስተባባሪ ሰብሳቢ ያሳውቃል፤
6. የሐብት ማሰባሰቢያ ደረሰኞች ከክፍለ ከተማ እስከ ብሎክ የሚካሄደውን ስርጭት የፋይናንስ ህግ ሥርዓትን ተከትሎ መፈጸሙን ተደራሽ መሆኑን ይከታተላል ይደግፋል፤
7. የክፍለ ከተማው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ከባንክ አካውንት ላይ በጣምራ ይፈርማል፤
8. የማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሐብት ማሰባሰብ ሂደቶችን በጥብቅ ዲሲፒሊን እንዲመራ ያደርጋል፤ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ መጠኑንና ዓይነቱን ይለያል፤

9. የሥራ አስፈጻሚውን አጀንዳዎች ያዘጋጃል፣ ስብሰባ ይጠራል፣ ውሳኔዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል ፣እንደአስፈሳጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠራ ይችላል፤
10. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው ያጠናክራል ፣ይከታተላል ፣ይደግፋል፣ ያስተባብራል፤
11. ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሐብት ማሰባሰብ ሂደቶችን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ይመራል፤
12. በክፍለ ከተማው ድጋፍ የሚሹ የማህበራዊ ችግር ተጎጂ የሆኑ ህፃናትን ሴቶችን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የተለዩበትን አግባብ መረጃ አያያዙን ይመረምራል፤ ትክክለኛነቱን ያረጋግጣል፤
13. በተጨማሪም በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባዔ ተግባራትን ይከናውናል፤

25. <u>የየክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ</u> የሚከተሉት ተግባርና ኃሳፊነት ይኖሩታል:-

1. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ አስተባበሪ ሴክተሮች ሰብሳቢ ይሆናል፤
2. የሥራ አስፈጻሚው ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣
3. በየበጀት ዓመቱ የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን የጉልበት እና እውቀት የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት ያቅዳል፣ በሥራ አስፈፃሚው አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ኮሚቴ ያጸድቃል፤
4. የተሰጡን ተግባራት በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይፈጸማል ስለክንውኑ ሪፖርት ያቀርባል፤
5. አረጋዉያን ለወጣቶች ልምዳቸውን የሚያካፍሉበትንና ወጣቶቹ ደግሞ የተለያዩ የእንክብካቤና የድጋፍ ተግባራትን የሚያከናውኑበትን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ እንዲተገበርም በትብብር ይሠራል፤
6. በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የትምህርትና ሙያ ሥልጠና እድል ለማግኘት ያልቻሉና ሥራ አጥ ወጣቶችን ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ችግራቸውን ለመፍታት መረጃቸውን አደራጅቶ ለሥራ አስፈጻሚው ያቀርባል ፣ይከታተላል ፣አፈጻጸሙን ሪፖርት ያቀርባል፣
7. የከተማው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት ከባንክ አካውንት ሳይ በጣምራ ይፈርማል፤
8. ብሎክን ማዕከል አድርጎ የተደራጀውን ማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረትን ቀጣይነት ባለው መልኩ ያጠናክራል፣ ይደግፋል፣ያስተባብራል፤
9. የክፍለ ከተማውን በብሎክ የተደራጁ ማህበረሰብ አቀፍ ኮሚቴዎችን ችግሮቻቸው የሚፈቱበት እና ጥያቄዎቻቸው ምላሽ የሚያገኙበት ሁኔታ ያመቻቻል፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲያጋዩጥሙ ለሥራ አስፈፃሚ አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ከመፍትሔ ሀሳብ ጋር ያቀርባል፤ ይከታተላል፤
10. የስራ አጥነት ችግር እንዲቀረፍ፤ እንዲሁም ማህበራዊ ችግሮች እንዲወገዱ ነዋሪው በባለቤትነት እና በፍላጎት እንዲመራው ሥራዎችን ይመራል ያስተባብራል፤
11. ከህብረተሰቡ የሚሰበሰብ ሀብት ፣አጠባበቅ፣ አጠቃቀም፣ አስተዳደር፣ ኦዲት ያስደርጋል፤
12. የወረዳውን ብሎኮች ሥራ ያግዛል፤ ከህብረተሰቡ የሚሰበሰቡ የገንዘብ መዋጮዎች ሥራ ሳይ መዋላቸውን ይከታተላል፣

13. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በብሎኮች መካከል በሚኖሩ ማናቸውም የማህበረሰብ ተሳትፎ ስራዎች እንዲቀናጁ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤

26. **<u>የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ፀሐፊ</u>** የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ አስተባበሪ ሴክተሮች ሰብሳቢ ይሆናል፤
2. የክፍለ ከተማውን ወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት መረጃዎች፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ አስፈላጊ ሰነዶችን ያደራጃል በአግባቡ ይይዛል ሲጠየቅም ያቀርባል፤
3. የክፍለ ከተማውን የብሎክ ነዋሪዎች ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤
4. የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ድጋፍ ፈላጊዎች በየጊዜው መረጃዎችን ያደራጃል ሲጠየቅም ያቀርባል ፣
5. የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ማህተም በጥንቃቄ ይይዛል፤
6. የወረዳዎችን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት በየብሎኩ በስፋት የሚነሱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአጀንዳ መካተቱን በማረጋገጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤
7. የክፍለ ከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ባንክ አካውንት ላይ በጣምራ ይፈርማል፤
8. የስብሰባ ጥሪዎችንና ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

27. **<u>የክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል ተግባርና ኃላፊነት፡-</u>**

1. ፍትህ ጽህፈት ቤት

ፍትህ ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ አስተባበሪ ሴክተሮች ሰብሳቢ ይሆናል፤

ለ. በክፍለ ከተማ ደረጃ የማህበራዊ ችግር ተጋላጮቾች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ይቀበላል ትክክለኛነት ይመረምራል ለቅሬታው ምላሽ ይሰጣል፤

ሐ. የማህበራዊ ችግር ተጋላጮቾች ልየታ ምልመላና መረጣ የድጋፍ አሰጣጥ ፍትሃዊነት ያረጋግጣል፤

መ. የሀብት አሰባሰቡን እና አጠቃቀሙን ፍትሃያዊነት ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

2. የጤና ጽህፈት ቤት

ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈፃሚ አስተባበሪ ሴክተሮች ሰብሳቢ ይሆናል፤

ለ. በበጀት ዓመቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭ የሆኑና በደማቸው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ ያለባቸውን መሰረት አድርጎ ያቅዳል፣ ያጸድቃል፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤

ሐ. የከተማውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፤

መ. ድጋፍ የሚሹ ሌች አይቪ/ኤድስ በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን መረጃ ያደራጃል ለምክር ቤቱ ያቀርባል ያጸድቃል፣ አሰራሩን ተከትሎ ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ድጋፍ እንዲደረግላቸው ክትትል ያደርጋል፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3. የፋይናንስ ጽህፈት ቤት

ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ለክፍለ ከተማው ሥራ አስፈፃሚ አስተባባሪ ሴክተሮች ሰብሳቢ ይሆናል፤

ሀ. የጥምረቱ ገቢና ወጪ የፋይናንስ አሰራር የተከተለ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ለ. የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ያሳትማል፤

ሐ. ክፍለ ከተማ በሥሩ ለሚገኙ ወረዳዎችና ብሎክ ጥምረቶች የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ያሰራጫል፤

ሠ. ከፍተኛ የሀብት ምንጭ ካለባቸው የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ድህነት ወደ ከፋባቸው የብሎክ ጥምረቶች ሀብት የሚዘዋወርበትን መንገድ ይቀይሳል፤

ረ. የክፍለ ከተማና ወረዳ ጥምርት ሂሳብ በራሱ ባለሙያዎች ኦዲት ያደርጋል፤ በተጨማሪም በውጪ ኦዲተርም እንዲያስደርጉ ያደርጋል፡፡

28. <u>የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ አመሰራረት</u> ጠቅላላ ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. ተጠሪነቱ ለወረዳው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይሆናል፤
2. የአስተባባሪ ኮሚቴ ሴክተር መስሪያ ቤቶች

ሀ. ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ......... ሰብሣቢ

ለ. ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ አጄንሲ .................. ም/ሰብሳቢ

ሐ. ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ......................................... ፀሃፊ

መ. ጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ .......................................... አባል

ሠ. ፍትህ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ......................................... አባል

ረ. ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ......................................... አባል

ሰ. በወረዳው በሚገኙ የብሎኩ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች....አባል

3. የወረዳው ሲቪክ ማህበራት:-

ሀ. የእድር ምክር ቤት ሰብሳቢ ......................................... አባል

ለ. የአረጋዊያን ማህበር ሰብሳቢ ....................................... አባል

ሐ. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ሰብሳቢ ............................... አባል

መ. የሴቶች ማህበር ሰብሳቢ ............................................ አባል

ሠ. የወጣቶች ማህበር ሰብሳቢ......................................... አባል

ረ. በወረዳው የሚሰራ የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅት .............. አባል

29. <u>**የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ**</u>

የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. በሰብሳቢው በሚደረግ ጥሪ በዓመት ሁለት ጊዜ ስብሰባውን ያደርጋል፤
2. የጥምረቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል የአፈጻፀም ይከታተላል ይቆጣጠራል፤
3. የአፈፃፀም ሪፖርት ያደምጣል ያፀድቃል፤
4. ኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፤ ያጸድቃል፤ ማስተካከያ እርምጃ ይስዳል፤
5. ሥራ አመራርና እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ይሰይማል ይሽራል፤
6. ለወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሐሳቦች ያመነጫል፤ በክፍለ ከተማ ሲፈቀድ ተፈፃሚ ያደርጋል፤
7. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የሐብት ምንጮችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሳል፤

30. <u>**የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ስራ አስፈጻሚ አመሰራረት**</u>

1. ተጠሪነቱም ለወረዳው ጠቅላላ ጉባኤው እና ለክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ይሆናል፤
2. ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ..................... ሰብሳቢ
3. ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ተወካይ ............. ም/ሰብሳቢ
4. በወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጡት ውስጥ ............................................................... ፀሐፊ
5. የሰላምና ጸጥታ ማስተባበሪያ ጽህፈትቤት ኃላፊ .......................... አባል
6. ጤና ጽህፈት ቤት ተወካይ .................................................. አባል
7. ፍትህ ጽህፈት ቤት ተወካይ .................................................. አባል
8. ትምህርት ጽህፈት ቤት ተወካይ .............................................. አባል
9. ሃይማኖት ተቋማት ህብረት ሰብሳቢ ........................................ አባል
10. ዕድሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ .................................................. አባል
11. ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ .................................................... አባል
12. አረጋውያን ማህበር ሰብሳቢ ................................................ አባል
13. የአካል ጉዳተኞች ማህበር ሰብሳቢ ...................................... አባል
14. የወረዳው የወጣቶች ማህበር ............................................. አባል
15. የወረዳው የታዋቂ ግለሰቦች ተወካይ .................................... አባል
16. የንግዱ ማህበራሰብ ተወካይ ............................................. አባል
17. እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃዉ ተጨማሪ የኮሚቴ አባላት ሊኖሩት ይችላል፡፡

31. **<u>የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ</u>**

የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና አንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

1. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ይተገብራል፣ የአፈጻፀም ሪፖርት ያቀርባል፤
2. ዓመታዊ ኦዲት ያስደርጋል፣ ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርቱ በማቅረብ ያጸድቃል፤
3. ከየብሎኩ የተለያዩ የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ ችግሮች የገጠማቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች በብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ እንዲለዩ በማድረግ መረጃወችን ይሰበስባል፤ እንደችግሩ መጠንና ስፋት እዲፈቱ ያደርጋል፤
4. ከተለየዩ አካላት ለማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የሚውል የፋይናንስ፣ የአይነት፣ የዕውቀት የጉልበት ሃብቶች ያሰባስባል፤
5. በወረዳው በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወረዳው የማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት አንድ የሂሳብ አካውንት ይከፍታል፤
6. የየብሎክ ጥምረት የሰበሰሰቡትን ገንዘብ በወረዳው ባንክ አካውንት ገቢ ያደረጉትን ደረሰኝ በመቀበል ከገቢ ደረሰኝ ጋር በማመሳከር አወራርዶ መዘግቦ መረጃ ይይዘል፤
7. በብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የተሰበሰበ ሐብት በገቢና ወጭ አርዕስት መሰረት መረጃዎች እንዲደራጁ ያደርጋል ፣ይደግፋል፤
8. የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አመራሮች የተለያዩ የአቅም ግንባታ፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
9. ከየብሎኩ ለማህበረሰብ አቀፍ እንክብከቤ ጥምረት ድጋፍ ሲያደርጉ የሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ይለያል የጉልበት የእውቀት የገንዘብ ሃብት የማሰባሰብ ሥራ ይሰራል፤ የተሰበሰበውን ገንዘብ ለጥምረቱ በተከፈተው አካውንት ገቢ ያደርጋል፤
10. ከተለያዩ አካላት ለማህበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ ድጋፍ የሚሰጡትን የፋይናንስ፣ የአይነት፣ የእውቀትና የጉልበት ሐብቶች ለየብሎኮቹ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ያከፋፍላል፣ ተደራሽ ስለመሆኑም ይከታተላል መረጃውንም አጠናክሮ ይይዛል፤
11. ለወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ ክብካቤ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሐሳቦች ያመነጫል በክፍለ ከተማው ጥምረት ሲፈቀድ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
12. የአጋርነትና የጥምረት ግንኙነት ሥራዎችን ይፈጽማል፤
13. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሂሳብ መዛግብት ሰነዶችን፣ የአባላት ዝርዝር መረጃዎችን፣ ወቅታዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭ የሕብተሰብ ክፍሎችን ዝርዝር በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤
14. በተጨማሪም በጥምረቱ ጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

32. **<u>የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት፦</u>**

1. ተጠሪነቱ ለወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ነው፤
2. ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ............ ሰብሳቢ
3. ሕብረተሰብ ተሳትፎ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ............ ምክትል ሰብሳቢ
4. በየክፍለ ከተማው ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና አንክብካቤ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ከተመረጡት ውስጥ .................................................. ፀሐፊ
5. ጤና ጽህፈት ቤት ኃላፊ .................................................... አባል
6. ትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ............................................ አባል
7. ፍትህ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ................................................ አባል
8. ፋይናንስ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ............................................ አባል

33. **<u>የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ ሰብሳቢ</u>**

የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለወረዳው ጥምረት ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

1. የጥምረቱን አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሥራና በጀት ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል ፣ ሥራ አስፈጻሚውን ኮሚቴ በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤
2. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል ፤ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፤
3. ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያፀድቃል፣ ድጋፉም እንዲደርሳቸው ክትትል ያደርጋል፤
4. ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው የማጠናከር፣ መከታተልና መድጋፍ እንዲያገኙ ለምክር ቤቱ ያሳውቃል፤
5. የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሐብት ማሰባሰብ ሂደቶችን ይከታተላል፤ መጠኑንና ዓይነቱን ይለያል ያለባቸውን ችግር /ክፍተት/ በመገምገም ይደግፋል፣ የማጠናከር ሥራ ይሰራል፤
6. የሥራ አስፈጻሚውን አጀንዳዎች ያዘጋጃል ፤ስብሰባ ይጠራል ፤ውሳኔዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
7. የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ርክክብ የፋይናስ ሥርዓቱን ጠብቆ እንዲከናወን የደርጋል፤
8. የወረዳውን የሂሳብ አካውንት በጣምራ ያንቀሳቅሳል፤
9. በወረዳና በብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ሀብት የማሰባሰብ ሂደት በጥብቅ ዲሲፒሊን እንዲመራ ያደርጋል፤ ይከታተላል ይደግፋል መጠኑን እና አይነቱን እየለየ ይመዘግባል፤
10. በወረዳው የተሰበሰበውን ገቢ በዓይነትና በገንዘብ ይቆጣጠራል፤ ወደ ባንክ ገቢ መደረግ ያለበት በየዕለቱ ገቢ መደረጉን ይቆጣጠራል፡፡

34. **<u>የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ ም/ ሰብሳቢ</u>**

ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

1. የሴክተር መስሪያ ቤቶች አስተባባሪ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
2. በየበጀት ዓመቱ የበጎ ፈቃደኛ ወጣቶችን የጉልበት እና እውቀት የማህበራዊ ድጋፍ አገልግሎት በአስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያቅዳል፣ ያጸድቃል፤
3. በሥራ አስፈጻሚው የተሰጡ ተግባራትን በማስተባበር ተግባራዊ ያደርጋል፣ ስለክንውኑ ሪፖርት ያቀርባል፤
4. አረጋዉያን ስወጣቶች ልምዳቸውን የሚያካፍሉበትንና ወጣቶቹ ደግሞ የተለያዩ የእንክብካቤና የድጋፍ ተግባራትን ሚያከናውኑበትን ሁኔታዎችን ያመቻቻል ፣እንዲተገበርም በትብብር ይሠራል፤
5. በተለያየ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የትምህርትና ሙያ ሥልጠና እድል ለማግኘት ያልቻሉና ሥራ አጥ ወጣቶችን ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ችግራቸውን ለመፍታት መረጃቸውን አደራጅቶ ለሥራ አስፈጻሚው ያቀርባል ፣ይከታተላል ፣አፈጻጸሙን ሪፖርት ያቀርባል፤
6. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል ፣ያስተባብራል፣ ያከናውናል ሪፖርት ያቀርባል፤

35. **<u>የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ ፀሐፊ</u>**

ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

1. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት መረጃዎች ፣ቃለ ጉባዔዎች ፣አስፈላጊ ሰነዶችን ያደራጃል ፣በአግባቡ ይይዛል ፣ሲጠየቅም ያቀርባል፤
2. የወረዳውን የብሎክ ነዋሪዎች ዝርዝር መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤
3. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ድጋፍ ፈላጊዎች በየጊዜው መረጃዎችን ያደራጃል ; ለሰብሳቢው ያቀርባል፤
4. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ማህተም በጥንቃቄ ይይዛል፤
5. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት በየብሎኩ በስፋት የሚነሱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአጀንዳ መካተቱን በማረጋገጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፤
6. የስብሰባ ጥሪዎችንና ወቅታዊ መረጃዎችን በወቅቱ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

36. **<u>የወረዳ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሴክተር መስሪያ ቤቶች ስራ አስፋጻሚ አስተባበሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. የጉባኤውን ውሳኔዎች ያስፈጽማል፤
2. የኮሚቴ አባላት የሆኑ አስፈጻሚ አካላት ተሳትፎ እንዲጠናከር ያደርጋል፤
3. ድጋፍ የሚሹ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን በምክር ቤቱ ያጸድቃል፣

4. ድጋፍ ሲያገኙ የሚገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የተቀሳጠፈ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ እንዲጠና በማድረግ ለጉባኤው ምክረ ሀሳብ ያቀርባል፤

37. <u>**የወረዳው ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አስፈጻሚ አስተባባሪ ኮሚቴ አባል**</u>

1. የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ኃላፊ

   ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

   ለ. በበጀት ዓመቱ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጋላጭ የሆኑና በደማቸው ውስጥ ኤች አይቪ/ኤድስ ያለባቸውን መሰረት አድርጎ ያቅዳል፣ ያጸድቃል፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤

   ሐ. የወረዳውን ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የዕለት ተዕለት ሥራ ያስተባብራል፣ ሪፖርት ያቀርባል፤

   መ. ድጋፍ የሚሹ ኤች አይቪ/ኤድስ ያለባቸውን እንዲለዩ ያስተባብራል፣ የተለዩትን መረጃ ያደራጃል፤ ለጥምረቱ ያቀርባል ያጸድቃል፣ አሰራሩን ተከትሎ ወደ ጎዳና ከመውጣታቸው በፊት ድጋፍ እንዲደረግላቸው ክትትል ያደርጋል ፣ ስለአፈጻጸሙም ሪፖርት ያቀርባል፤

   ሠ. ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት አደረጃጀትንና አሰራርን በየጊዜው የማጠናከር ፣ መከታተልና ድጋፈ እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

   ረ. የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የሐብት ማሰባሰብ ሂደቶችን ይከታተላል፣ ያለባቸውን ችግር ይለያል፣ ይደግፋል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ያገኙትን ድጋፍ መረጃ ይይዛል፣ ያስተባራል፡፡

2. የወረዳው ፍትህ ጽ/ቤት

   ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊናት ይኖሩታል፤

   ለ. በወረዳ ደረጃ የማህበራዊ ችግር ተጋላጮችች የሚያቀርቡትን ቅሬታ ይቀበላል ትክክለኛነት ይመረምራል ለቅሬታው ምላሽ ይሰጣል፤

   ሐ. በወረዳ የማህበራዊ ችግር ተጋላጮችች ልየታ ምልመላና መረጣ የድጋፍ አሰጣጥ ፍትሃዊነት ያረጋግጣል፤

   መ. የወረዳ ሀብት አሰባሰቡን እና አጠቃቀሙን ፍትያዊነት ይከታተላል፣ አስፈላጊ ሁኖ ሲያገኘው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

3. የፋይናንስ ጽ/ቤት

   ሀ. ተጠሪነቱ ለጥምረቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

ሰ. የጥምረቱ ገቢና ወጪ የፋይናንስ አሰራር የተከተለ እንዲሆን የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ሐ. የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ለብሎክ የጥምረት የሚደረጉ ስርጭቶች በተገቢው በገቢና ወጪ አሰራር መሠረት መሆኑን ይከታሳል፤

መ. መካከለኛ የሀብት ምንጭ ካለባቸው የማህበረሰብ ክብካቤ ጥምረት ድህነት ወደ ከፋባቸው የብሎክ ጥምረቶች ሀብት የሚዘዋወርበትን መንገድ ይቀይሳል፡፡

38. <u>የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አደረጃጀት</u>

የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ የብሎኩ ነዋሪ ነው፡፡

39. <u>የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፤
2. የብሎክን ጥምረቱን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል የአፈጻፀም ሪፖርት ያዳምጣል፤
3. የብሎኩን ጥምረት ዓመታዊ ኦዲት ሪፖርት ያዳምጣል፤ ያጸድቃል፤
4. የብሎኩን ጥምረት ሥራ አመራርና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎችን ይሰይማል ይሽራል፤
5. ዘለብሎኩ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሐሳቦች ያመነጫል በወረዳው ጥምር ጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጥምረቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ያደርጋል፤
7. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የሐብት ምንጮችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሳል፡፡

40. <u>የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ ድጋፍና እንክብካቤ ጥምረት ሥራ አመራር አደረጃጀት</u>

ተጠሪነቱ ለብሎኩ ነዋሪ ወይም ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ በዋነኛነት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የብሎኩ መሠረታዊ እድሮች አመራር ወይም መሰረታዊ እድር ከሌለ በብሎኩ ጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጥ ተወካይ ........................................ ሰብሳቢ
2. ከታዋቂ ሰዎች ተወካይ ...................................... ምክትል ሰብሳቢ
3. የወጣቶች ማህበር ተወካይ .............................................. ፀሐፊ
4. የሴቶች ማህበር ተወካይ ............................................ ገንዘብ ያዥ
5. የአረጋውያን ተወካይ ................................................ ሂሳብ ሹም
6. የሐይማኖት አባቶች ተወካይ ..................................... ንብረት ያዥ
7. የአካል ጉዳተኞች ተወካይ ............................................... አባል
8. የባለሐብቶች ተወካይ ............................. ........................ አባል
9. የወጣቶች ተወካይ ........................................................ አባል
10. በብሎክ ነዋሪዎች ወይም በጠቅላላ ጉባኤ የሚወከሉ ሦስት የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ይኖሩታል፡፡

41. <u>የብሎክ ሥራ አመራር ተግባርና ኃላፊነት</u>

በብሎኩ ኑዋሪዎች ታማኝና ተቀባይነት ያላቸው እንዲሁም ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የሚችሉ አባላትን የያዘ እና ተጠሪነታቸው ለጠቅላላ ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ጠቅላላ ጉባዔውን ይሰበስባል፤
2. የብሎኩን ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ያፀድቃል፣ ይተገብራል፣ የአፈጻፀም ሪፖርት ያቀርባል፤
3. ዓመታዊ ኦዲት ያስደርጋል፣ ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርቱ እንዲቀርብ ያደርጋል፤ ያስጸድቃል፤
4. ንዑሳን ኮሚቴዎች አባላትን ያሥመርጣል፣ ሰብሳቢወችን ይሰይማል፣ ያሰራል፤
5. የብሎኩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያጸድቃል፣ ይህንን መሠረት አድርጎ ውሣኔዎችን ያሳተላልፋል፤
6. ለብሎኩ ማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት አሠራርና መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ሐሳቦች እንዲወጡና ተፈፃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
7. የንዑሳን ኮሚቴዎችን ይመራል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣
8. ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚረዱ የሐብት ምንጮችንና ስትራቴጂዎችን ይቀይሳል፤
9. የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልቶችን በመቀየስ ይተገብራል፤
10. የአጋርነትና የጥምረት ሥራዎችን ከውጭም ሆነ ከውስጥ ትሥሥር ይፈጽማል፣
11. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የጥምረቱን መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ያደርጋል፤
12. ሰነዶችን ፣ መረጃዎችን በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤

42. <u>የቴክኒክ ንዑሳን ኮሚቴዎች</u>

በብሎክ ደረጃ የሚዋቀሩ የቴክኒክ ንዑሳን ኮሚቴዎች ተጠሪነታቸው ለብሎክ ሥራ አስፈጻሚ ሁኖ የሚከተለው አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡-

1. የሐብት ማሰባሰብና የመሰረተ ልማት ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢው የሥራ አስፈጻሚው ገንዘብ ያዥ ሁኖ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሁለት አባላት ይኖሩታል፤
2. የሰላምና ጸጥታ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢው የሥራ አስፈጻሚው ምክትል ሰብሳቢ ሁኖ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሁለት አባላት ይኖሩታል፤
3. የትምህረትና የቅስቀሳ ንዑስ ኮሚቴሰብሳቢው የሥራ አስፈጻሚው የወጣቶች ተወካይ ሁኖ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሁለት አባላት ይኖሩታል፤
4. የምዝገባ ፣ምልመላ፣ መረጣ፣ መረጃና የድጋፍ አሰጣጥ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢው የሥራ አስፈጻሚው ፀሐፊው ሁኖ በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡

43. <u>የብሎክ የቴክኒክ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የሀብት ማሰባሰብ እና መሰረተ-ልማት ንዑስ ኮሚቴ

ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፤

ለ. የአካባቢውን እና የነዋሪዎችን ነባራዊ ሁኔታ በማጥናት የሀብት ምንጮችን ልየታ ሥራ ያከናውናል፤

ሐ. በልየታው መሰረት የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ያከናውናል፤

መ. በግንዛቤ ማስጨበጫው መግባባት በተፈጠረው መሰረት የጉባዔው አባላትን ወርሐዊ መዋጮ እና ሐብት በጉልበት ፤ በገንዘብ ፣ በእውቀት በተዘጋጀው የገቢ ደረሰኝ ዝርዝር መሰረት ያሰባስባል፣

ሠ. የተሰበሰበውን ገንዘብ በብሎኩ አካውንት ገቢ ያደርጋል፤ ዓይነትን ፣ ጉልበትንና አውቀትን በገንዘብ በመተመን መረጃ ያደራጃል፤

ረ. ስተሰበሰበበት ዓላማ መሰረት ሥራ ላይ ስለመዋሉ ዝርዝር የወጭ መረጃ ይይዛል፤

ሰ. አጠቃላይ የሐብት አያያዝ፣ ገቢና ወጭ የፋይናንስ ሥርዓትን የተከተለ እንዲሆን ያደርጋል፤

ሸ. የስራ ክንዉን ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፡፡

2. የመረጣ ልየታ ድጋፍ አሠጣጥ ንዑስ ኮሚቴ

ተጠሪነቱ ለብሎክ ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያፀድቃል የአፈጻፀም ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ. ድጋፍ የሚሹ የብሎኩ ነዋሪዎች እንደ ችግራቸው መጠንና ፍላጎት መስፈርቱን መሰረት አድርጎ ይመዘግባል፣ ይመለምላል፣ ይመርጣል፣ ለሥራ አስፈጻሚ አቅርቦ በማስወሰን በጠቅላላ ጉባዔ ያጸድቃል፤

ሐ. ለተለያየ ድጋፎች በተመለመሉትና በተመረጡት ላይ ቅሬታዎችን ለመቀበል ሥርዓት ይኖረዋል፤

መ. ለድጋፍ የተመለመሉትንና የተመረጡትን አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያደርጋል፤

ሠ. የተደረገውን ድጋፍ በዓይነት፣ በጉልበትና በገንዘብ ዝርዝር መረጃ ይይዛል፣

ረ. በተዘዋዋሪና በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ የሚረዱትን በመስፈርት በመለየት ለሥራ ስፈጻሚ አቅርቦ ያፀድቃል፤ ሲፈቀድ በተሰበሰበሰው የሐብት መጠን ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሰ. በሥራ አስፈጻሚው የተወሰኑ ውሳኔዎችን ተግባረዊ ያደርጋል፡፡

3. የትምህርትና ቅስቀሣ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለብሎክ ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ይተገብራል ፣ የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ. ነዋሪዎች የማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤ ጥምረቱን እንዲያጠናክሩ ግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

ሐ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን (አደዛዥ ዕፅ ተጠቃሚነትና ዝውውር፣ ሕገወጥ የሰወች ዝውውር እና ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ) ለመካላከል በአካባቢው የሚኖሩ ባለሙያዎችን በመጋበዝ የግንዛቤ ማሳደጊያ በመስጠት የአመለካከትና የባሕሪ ለውጥ እንዲመጣ ያደርጋል፤

መ. ምሁራንን፣ ታዋቂ ግለውሰቦችንና የሃይማኖት መሪዎችን በመጠቀም በብሎክ የማህበራዊ ችግሮች የሚቀንሱበትንና ነዋሪዎች የተሻለ ማህበራዊ ሕይወት እንዲኖሩ ያስተምራል፤ ይቀሰቅሳል፤

ሠ. ድህነትን ለመቀነስና ለማጥፋት ስትራቴጂዎችን በመቀየስ የተለያዩ አነሳሽ ጽሁፎችንና መልዕክቶችን በማዘጋጀት እና በአመቺ ሁኔታ በማቅረብ የህብረተሰቡን ተነሳሽነት ያሳድጋል፤

ረ. ለሥራ እድል ፈጠራ የሚያግዙ የክህሎት፣ የእውቀትና የአመለካከት ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና በመቀየስ እንዲሰጥ ያደርጋል፤

4. የሰላምና ፀጥታ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለብሎክ ሥራ አስፈጻሚ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ይተገብራል ፣የአፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

ለ. የብሎኩ ነዋሪዎች የፀጥታና የሰላም አደረጃጀትና አሰራር በመፍጠር የአካባቢያቸውን ሰላም እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

ሐ. ከአካባቢው የመንግስት ፖሊስና የፀጥታ መዋቅሮች ጋር በመተሳሰር የብሎኩን ነዋሪዎች ደህንነት እንዲጠበቅ ይሠራል ፣ ያስተባብራል፤

መ. ለሰላምና ለፀጥታ አስፈላጊ የሆኑትን ፋይናንስ ፣ ማቴርያልና ቁሳቁስ በመለየት የብሎኩ ነዋሪዎች እንዲያሟሉ በዝርዝር ለሚመለከተው ያቀርባል፤

ሠ. ለነዋሪዎች አስጊ የሆኑ ቦታዎችንና ድርጊቶችን በመከታተልና በመለየት ለሚመለከተው የመንግስት አካል ያሳውቃል፣ ለስአፈጻጸሙም በጋራ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

ረ. ከአካባቢው የመንግስት ፖሊስና የፀጥታ መዋቅሮች ጋር በመተሳሰር ለብሎኩ የሚሆን የጥበቃና የጸጥታ የሰው ኃይል እንዲቀጠር ያደርጋሉ፤

5. የቅሬታና አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ተግባና ኃላፊነት

ሀ. በብሎኩ ማህበረሰብ እንክብካቤ ጥምረት አሰራር ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይቀበላል፤

ለ. የቀረበለትን ቅሬታ ትክክለኛነት ያጣራል፤

ሐ. የቅሬታውን ምላሽ በፅሁፍ ለቅሬታ አቅራቢው ለወረዳው ሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፤

መ. የቅሬታውን ምላሽ መረጃ አደራጅቶ ያስቀምጣል፤ መረጃው ሲፈለግም ያቀርባል፡፡

44. **<u>በብሎኩ ውስጥ የሚኖሩ የጥምረቱ አባላት መብትና ግዴታ፡-</u>**

1. በብሎኩ ውስጥ የሚኖሩ የጥምረቱ አባላት መብት፡-
   ሀ. በብሎኩ በሚመሰረተው የማህበረሰብ አቀፍ ጥምረት በሚሰጡ አገልግሎቶች የመጠቀም መብት፤
   ለ. በጠቅላላው ጉባኤ ላይ በመገኘት ድምጽ የመስጠት፣ የመመረጥና የመምረጥ፤
   ሐ. የጥምረቱ መተዳደሪያ ደንብና አገልግሎቶች እንዲሻሻሉ ሀሳብ የመስጠትና የማቅረብ፤
   መ. ጥምረቱ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ዙሪያ መረጃ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፤
   ሠ. በብሎክ የሚመለመሉ ተጠቃሚዎችን የማጣራት መብት፡፡
2. በብሎኩ ውስጥ የሚኖሩ የጥምረቱ አባላት ግዴታዎች፡-
   ሀ. የጥምረቱን መተዳደሪያ ደንብ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግና መተግበር፤
   ለ. የጥምረቱን የአባልነት ክፍያ መክፈል፤
   ሐ. ጥምረቱ እንዲጠናከር በቅን መንፈስ እውቀትና ጉልበት ድጋፍ የማድረግ፤
   መ. የጥምረቱን ሀብት/ንብረትና ገንዘብ መጠበቅ፤
   ሠ. በጥምረቱ የሚሠጡትን ተግባርና ኃላፊነት የማከናወን፤
   ረ. በስራ ምክንያት ያወቀውን መረጃ ሚሥጥር የመጠበቅ፡፡

45. **<u>የብሎክ ማህበረሰብ አቀፍ እንክብካቤ ጥምረት የቁጥጥርና የኦዲት ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ፡-</u>**

ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባርና፡-

1. የብሎኩን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግብርና ኃስፊነቱን መወጣቱን ይከታተላል፤
2. ከብሎኩ ነዋሪዎችና ከሌሎች አካላት የተሰበሰበ ሐብትን በአግባቡ ስለመያዙና ስተባለው ዓላማ ስለመዋሉ ይከታተላል፤
3. ከብሎኩ ነዋሪዎችና ከሌሎች አካላት የተሰበሰበ ሐብትን የፋይናንስና የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ሪፖርት ለጠቅላላው ጉባዔ ያቀርባል፤
4. የብሎኩን ነዋሪዎች የሚመለከቱ ሕጎችና መተዳደሪያ ደንቦች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል ፤ ተጥሰው ሲገኙ እንዲታረም ለሚመለከተው ያቀርባል፤
5. በጠቅለላ ጉባዔ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ተግባራዊነት ይከታተላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## የገቢ ምንጭ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት

46. **የጥምረቱ የገቢ ምንጮች**

    1. ከአባላት በቋሚነት ከሚደረግ ወርሃዊ መዋጮ፣
    2. ከተለያዩ አካላት ከሚገኝ ድጋፍ፣
    3. በተለያዩ ገቢ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች የሚገኝ ገቢ፡፡

47. **የሀብት አያያዝና አጠቃቀም**

    1. የማህበረሰብ ድጋፍና ክብካቤና ጥምረት ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰበውን ሀብት ለብክነት እንዳይጋለጥ ግልፅ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ይከተላል፣
    2. የጥምረት ምክር ቤቶች የራሳቸዉ የሆነ የባንክ አካውንት የሚኖራቸዉ ሲሆን ሰብሳቢው፣ፀሐፊው እና ሒሳቡ ሹም ጣምራ ፊርማ ሂሳብ እና ንብረት የሚንቀሳቀስ ሲሆን አጠቃላይ አሠራሩ በመተዳደሪያ ደንቡ ይገለጻል፣
    3. በተለያዩ አግባብ የሚገኝ ንብረት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ድጋፍ ለሚሹ የብሎኩ ነዋሪች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፣
    4. በአስቸጋሪ ኑሮ ሁኔታ ላይ ለሚገኙና ሠርተው መለወጥ ለሚችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ ከተሰበሰበው ሐብት የተዘዋዋሪ ብድር ገንዘብ መጠን 40% ሲሆን ቀሪው 60% የቀጥታ ተጠቃሚዎች ይሆናል፡፡ዝርዝሩ በመተዳደሪያ ደንቡ ይገለጻል፣

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

48. **ስለሒሳብ መዛግብት አያያዝ**

    1. በየደረጃው ያሉ የማህበረሰብ አቀፍ ምክር ቤቶች የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይኖራቸዋል፡፡
    2. የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በውስጥና በውጭ ኦዲተር በየበጀት ዓመቱ ያስመረመራሉ፡

49. **የመተባበር ግዴታ**

    ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

50. **ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

    ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

51. **<u>መመሪያው ስለማሻሻል</u>**

ቢሮው ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

52. **<u>መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበትና ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ጥር፡ 2015 ዓ.ም

ዶክተር ሐና

የሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ